# ኢትዮጵያዊነት

## በአስራምዕት ኢትዮጵያ

## ከኢትዮጵያዉያን በኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን

**_መግቢያ_**

ይኽ መጣጥፍ ወረቀትና ቀለም ሳይገናኙ በፊት በተለያዩ አህጉርና ሀገር ግዛቶች ዛሬ በሕይወት ካሉና ከለሉም ጋር ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን ስደተኛው ወገናችንን በሲምፖዚየም አኳያ አሰባስቦ፤ ዲፋክቶ ተቋማት ማዋቀርና ኢትዮጵያዊያንን በየሙያቸው ማደራጀት ነበር። ውጥኑ በሃሳብ ሲላወስ በአለበት ወቅት ካውንስል ኦፍ ኤልደርስ (Council of Elders) በሚል ንዑስ ዘርፍ የዕ ድሜ ባለጠጋ፤የተለያየ ዕውቀት፣ ተመክሮና ዝንባሌ ያላቸውን ዜጎች ብሔራዊ "ቲንክ ታንክ መሣይ" (Think tank) ለማዋቀር የመጀመሪያው ትውውቅ (በቴሌኮንፍረንስ) ተደረገ፤ የሚቀጥለው መርሃ-ግብር የታቀደው ደግሞ በአንኳር ጉዳዮች (እርቀ ሰላም ከሕዝብ ለሕዝብ፣ ራስ ደጀን ሕዝባዊ ሠራዊትና ሽግግር መንግሥት ዝግጅት) ለመምከርና ለመዘከር ሁኖ ሳለ ውጥኑ ተጨናገፈ። በእስራ ምዕት ኢትዮጵያ (ሚሊኒየም) መባቻ ወቅት በሃገራችን ጉዳይ ጽሑፍ እንዲቀርብ ጥሪ ሲደረግ በቴክኒክ ጉድለት ከገደቡ ትዝለቅ እንጂ መጣጥፏ ተሞጫጭራ ብዙ ወዳጅ እጅ እስከሚያያት ሰነባብታለች። ይኽ በእንዲህ እንዳለ በዲሲ አካባቢ ሲምፖዚየም ኢትዮጵያዊያን ያደርጋሉ ተብሎ ተደረገ። የዚህ ሲምፖዚየም ታዳሚዎች ጠላት ወዳጅ ሳይለይ እንደተካሄደ በአጽንኦት ስንከታተል፤ በወያኔ ፔይሮል (Pay roll) በተለያዩ መድረኮች ጥብቅና የሚቆሙ ፈረንጅ እንደራሴዎቹም የታዳሚው አካል እንደነበሩ ነብይነትን አይጠይቅምና በእጅጉም በምሬት አዘንን!! ፈታኝ ጥረቶች የጠየቁ ቁልፍ ቅድመ ሁኔታዎችን (አሁንም የሚያሳስበን) ስትጠብቅ የነበረች ይኽች ጽሑፍ ለንባብ እስከበቃች ቅርብ ቀናት ድረስ ብቅ ያሉ ክስተቶችን በማካተት ደልባ እዚህ ደርሳለች። የብልሃተኛ ልጅ በተመሳሳይ ጉዳይ ዳግም አይሳሳትምና ከእንግዲህ በኋላ የኢትዮጵያውያን ሲምፖዚየም የወገን ታዳሚ ብቻ፤ ሕዝባችን ከጠላት ራሱን የሚከላከልበትን ዘዴ የሚመክርበትና የሚዘክርበትን ሠፊር ንቁና ጥንቁቅ ታዳሚ እንዲሆን ግድ ነው።

በታጋሽነትና በጀግንነት ገድሉ በታሪክ ገጾች ሁሉ የሚዘከርለት የኢትዮጵያ ህዝብ በመሰሪ የታሪክ ጠላቶቹ ንቁ ደባ አንገቱን እንዲደፋ ብሎም እንዲከስምና ምሳር እንዲበዛበትም የተደረገው ኢትዮጵያዊነት በትግስትና ብርቱነት ተቋቁሞ እዚህ የታሪክ እርከን ላይ ደርሷል። ያ ሁሉ ኩታ ገጠም የጠላት መንጋ ያሴረው የጎጠኝነት ፖለቲካ ሳይበግረው በቅድሚያ በድንበር ጦርነት ሰበብ በተከሰተ ግጭት እየደማም ኢትዮጵያዊነት አንገቱን ቀና በማድረግ ከዚያም ሦስተኛዉን ሕዝባዊ ምርጫ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ለነዚህ ጠላቶቹ ቅዠት ሆነ፤ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ሲወድቅ ሲነሳና ሲደማ ምንም ምድራዊ ሃይል በማይበግረው የእድገት እርከን ላይ ጎልብቶ ይገኛል፤ የመጨረሻው ወሳኝ ድል ግን ገና ነው። ለዚህ ታሪካዊ ድል ለመብቃት ምን ይጠበቅብናል?

የአንድ ባለረጅም ታሪክ ሐገር ሕዝብ በመሆናችን፤ የሰው ልጆች ዘር መገኛ ሐገር አካል በመሆናችን፤ በዜግነታችን፣ በሐገራችን ሉዓላዊነትና በሕዝቧ አንድነት ላይ እየተፈጸመ ያለውን ዓለም አቀፍ ሴራ በምድራዊ ፍርድ መድረክ ለመጠየቅና ሰላቢ ተዋንያንን ገሃድ በማውጣት እንዳወቅንባቸው እንዲያውቁ በግልጽ ቋንቋ ማስተጋባት ያለብን ብንዘገይም ዛሬ ነው። ጄኖሳይድ በኢትዮጵያ ኦፍሴላዊ ክስ ለመመስረትም ዝግጅቱ ቢዘገይም አሁን ግድ ይሏል። የኢትዮጵያን ታሪካዊ ደመኞች መንጋ በመስኮት እየተመለከትናቸው በሐገራችን ሉዓላዊነት መናጋት ከመጠየቅ እንደማይጸዱና በተለያየ ሰንካላ ምክንያት የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ ድጋፎች (የንዋይና ወታደራዊ ሎጀስቲኮችን) በአስቸኳይ እንዲያቆሙ በጥያቄዎች ማስገደድ ብንዘገይም ዛሬ ነው። ነገር ግን በጠባቡ መርፌ ቀዳዳ የምናነጣጥረውና ያለ የሌለ ሕዝባዊ ክንዳችንን ከኢትዮጵያዊ ወገናችን ጋር በማስተባበር ወያኔንና ሻዕቢያ፣ ለሎችም ውስጥ በቀል ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ግብረ አበሮቻቸውን በኅብረ-ብሔር አልሞት ባይ ተጋዳይነት መፋለም ቢዘገይም ዛሬ ነው።

የነፃነት ተጋድሎ እኮ የሐገርና የሕዝባችንን ሉዓላዊነት ለማስከበር የሚደረግ ተጋድሎ ነው፤ የአርነትና ሕልውና ተጋድሎ እንጂ ሌላ መለስተኛ ጥያቄ ሊሆን በፍጹም አይችልም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር እንጂ የሌሎች ኩምባያ ማደናገሪያ ዘፈን " ዲሞክራሲ " ሊሆን ፍጹም አይቻልም። ዲሞክራሲ በነፃነት የተዋጠም፤ ይዋጣልናም!! በቅጥረኛ ወራሪ ኃይል ተከባ እየደማች ያለች ሐገር፣ የኮራና የተባ ታሪክ ያለውን ህዝብ በእኩይ ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ደባ ለብዙዓን ረሃብና በሽታ በመዳረግ ስብዕናው እንዲሰለብ የሚሸረበውና የሚተገበረው ሴራ የሚከሽፈውና ሁለንተናዊ የሃገር ደህንነት የሚረጋገጠው እኮ ሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቀፈ ሕዝባዊ ሠፈር ከወዲሁ ማደራጀት ሲቻል ነው። ይህ ግዙፍ ሃላፊነት የወደቀው ስብዕና በሚሰማቸው የኢትዮጵያ ልጆች ትከሻ ላይ ነው። ለሌላ ትውልድ የሚተው ጉዳይ አይደለም። በኢትዮጵያ ስትራተጂክ ጠላቶች ረቂቅ ቀመር ኢትዮጵያና ሕዝቧ ኢላማ መስቀላቸው ውስጥ በመገኘታችን ያሰፈሰፈውን የጠላት ኃይል የምንቋቋመው በውስን የፖለቲካ ድርጅቶችና ፓርቲዎች ወይም በባእዳን አስተባባሪነት ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ በማስተባበር ብቻ ነው። ድርጅታዊ አሠራር በተከተለ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ (Popular Movement) ራስን ከግድያ በመከላከል፤ በአመጽና ሌላም! አማራጭ የለም።

ለዚህም ዛሬ ጠላትን መለየት ግድ ነው!!! የኢትዮጲያዊነት ጠላቶች በቅርበት ወያኔና ሻዕቢያ ብሎም ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ውስጥ-ብቀል ኃይሎች ከነግብረአበሮቻቸው፤ በርቀት ደግሞ ታሪካዊ ጠላቶቿ ጥቂት አይደሉም። ጠላትን እጥር ምጥን ባለ ቋንቋ ባለመተርጎም መፋለም ድልን የትየለሌ ያራዝማል፤ የንዋይ፤ የሎጀስቲክና የሰው ግብረሃይል እንዲሟሽሽና በከንቱ እንዲባክን ያስገድዳል። ድል የመስዋዕትነት ዋጋ ነችና እነኚያ የበቁ ጀግኖቻችንን የነ በላይ ዘለቀ፣ አሉላ አባ ነጋ፣ ሻቃ በቀለ ወያና የአያሌ ሰማዕታት ኢትዮጵውያን ተምሳሌነትና በጀግንነት ኮቴያቸው እየተመራን ዳግማዊ የአድዋ ድል በኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በድጋሚ እንዲመዘገብ ምእራፉ "ያልተጻፈበት ክፍት ገጾችን" እንደያዘ እየጠበቀን ነው። ዛሬ ሐገራችን የገጠማት ችግር በወደር አልባነቱ መለኪያና መስፈሪያ ያልተገኘለት ዘርፈ ብዙ ነው። ይህ ችግር ከፖለቲካ ቀውስነት ዘሎ በማህበረሰባችን፣ በኢኮኖሚው ዘርፍ፣ በባህልና ቅርሳቅርስ ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶች፤ በአብያተክርስቲያናት፤ በሆስፒታሎችና በሌሎችም ነባር ተቋማት ላይ በመዝመት በታሪካዊ ጠላቶቿ እኩይ ባሕርይ ምስቅልቅሏ እንዲወጣ በመደረጉ ከነፃነቱ ተጋድሎ ጎን ለጎን በተሃድሶና ግንባታ፣ በልማትና እድገቱ መስኮች የሚደረጉ ተጋድሎዎች በሰከነ አእምሮ፣ ወደር በሌለው ትዕግስትና ቁርጠኝነት ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል በተዘጋጁ ኢትዮጵያዉያን፣ በየትም አካባቢ ለዲፋክቶ ተቋማት እውንነት ቅድመ ዝግጂቱ ከወዲሁ መጀመር አለበት። የዉዴታም ግዴታ ነዉና።

የኢትዮጵያ ችግሮች በኢትዮጵያውያን በጥልቀት እንዲጠኑ፣ መፍትሄዎች ከኢትዮጵያውያን እንዲመነጩ ዘርፈ ብዙው መስዋዕትነት የሚወልደውን ድል ጠቀሜታነቱን ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን በዘላቂነትና በአስተማማኝነት እውን ለማድረግ ልዩ የትግል ፓራዲያም ግድ ይሏል። ይኸውም በተለያዩ ተቃዋሚ መስመሮች ተሰልፈው የሚታገሉ ፀረ-ወያኔ ወገኖች ሠፈር ጥላቻና ቂም በቀል በመካከላችን እንዳይፈጠርና የኋላ ኋላ አደገኛ ግጭት ተከስቶ ባዕዳን ሐይሎች በሰላም ማስከበር ሰበብ እንዳይወሩንና "ግብዓተ-መሬት ለኢትዮጵያ ትልማቸው" ሜዳዉን እንዳናመቻች ከጊዜ በአሻገር ማገናዘቡና መጠንቀቁ የብልሆቹ ጥንታዉያን ጀግኖች ወላጆቻችንን ፈር መከተል ግድ ይሏል። አሊያ ግን የማንቆጣጠረው አይቀሬ ሁከት እንዲከሰት ሆኖ ለማንኛዉም ፀረ-ኢትዮጵያ ጠላቶች ለፈጸሙትና ለሚፈጽሙት ዘር የማጥፋት ወንጀሎች (ጄኖሳይድ) ተከኒካል ሽፋን እንዳንስጥ ግዙፍ ሐላፊነት እንደተሸከምን ከወዲሁ ማጤን ግድ ነው።

በተለያዩ ነባር ሃይማኖቶች ተከታይ ምዕመናን፣ በተለያዩ የሙያ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ግለሰቦች፣ የሲቪክ ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፓርቲዎች፣ አንድም ሁለትም በመሆን፤ እንዲሁም ኢትዮጵያዊነታቸውን በመነጠቃቸው የሚያንገበግባቸዉ የባሕረ ነጋሽ ተወላጆች ኢትዮጵያውያንና ባለፉት የኢትዮጵያ መንግስቶች በተለያዩ ሙያና ሥራ ዘርፎች ያገለገሉ፣ በሕዝብና ሀገር ላይ ወንጀል ያልፈፀሙ ግለሰቦችን ሁሉ ያቀፈ ***"የኢትዮጵያዉያን ሲምፖዚየም"*** በአስቸኳይ ተጠርቶ በሐገራችን ሉዓላዊነትና

በሕዝቧ አንድነት ላይ ያተኮረ፣ በሐገሪቷ ደህንነትና በሕዝቧ አርነት ዙሪያ ከቅድመ ሁኔታዎችና ድርድሮች ጥያቄ ነጻ የሆኑና ብሔራዊ ጠቀሜታዎችን ያካተቱ ጉዳዮች በሚያስተማምን ሕዝባዊ ስሚንቶ መሠረቱን ለመዘርጋት ከላይ በተጠቀሱት ዲፋክቶ ተቋማት ግለስቦችን እንደየሙያቸው በሥራ ክፍፍል ለማዋቀር እንዲቻል የኢትዮጵያዊያን ስብሰብ ድርጅቶች ባሉበት አካባቢ በቤተሰብና ጓደኞች ዘንድ ይህን ***"የኢትዮጲያውያን ሲምፖዚየም"*** ተግባራዊ ለማድረግ የሚያሰባስብና ለመተግበር የሚያስችል ዲያሎግ መክፈት ማለፊያ ጅማሮ ነው። በሂደትም በሚመነጩ ሐሳቦችና ያልተጠበቁ ሁኔታዎች በሚፈጥሩት ክስተቶች ዲፋክቶ ተቋማቱ አዎንታዊ ሕዝባዊ ይዘት እንዲኖራቸው ስምፖዚየሙ ማለፊያ አድራሽ ሐዲድ በመሆን ያገለግላል።

የኢትዮጵያውያን ሲምፖዚየም ዘርፈ ብዙ "ዲፋክቶ ተቋማት" እንዲኖሩትና አስፈላጊውን ኃይል በየሙያውና ዝንባሌው አንዲካተት ብሎም በየምድብ ዘርፉ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በመጀመር ሁለገብ "የትግል ፓራዲያም" ለመተለም በግለሰቦችና በድርጀቶች በታቀፈ የዜጎች ስብሰባ አንድ የጋራ ህዝባዊ ጊዜያዊ የአመራር አካል በመፍጠር በጠላት ይፋ የታቀደው የመቶ ዓመታት፤ ይፋ ያልሆነም ችግር በመቶ ወሮች ሁለገብ ሥራዎች፣ በጥናትና ምርምር የተገነባ ዕቅድ በማካተት፣ በሙያና ተመክሮዎች፣ በሃብትና በተፈጥሮ በእግዚአብሔር ቸርነት የታደሉትን ጸጋ በማስተባበር የኢትዮጵያዊነትን ትንሳዔ ያለምንም ጥርጣሬ ያፈጥናል፤ ያረጋግጠዋልም። ለጠላቶቻችን ግን ቅዠት ይሆናል።

ያለፉት የትግል ምዕራፎች የመዘገቡትን ክስተቶችና ሁኔታዎች በተከሰቱበት አስገዳጅ ወቅት ወይም ማለፊያ ገጠሜዎች የአሳደሩትን ጫና በሰከነ ስልት ተሰልቶና ተቀምሮ በማንጠር ዛሬና ነገ ለሚከናወኑ ተግባራት ትምህርታዊ ጠቀሜታ ከሌላቸው ጎጅነታቸው በቀላሉ ሊታይ አይገባም። በዘረኝነት ደዌ በተበከሉና በጎጠኝነት ፖለቲካ በታወሩ እብሪተኞችና የፈረንጅ እንደራሴዎች ቅጥያ፤ በሌላ አገዛዝ ስር እንዳንወድቅ መጠንቀቅና መዘጋጀት ቢዘገይም ዛሬ ነው። ለምሳሌ በሐገር ቤት የቅርብ ጊዜ የትግል ትውስታ ኅብረ-ብሔር አልባ ሙከራዎች ቢከሽፉም "የቀስተ ዳመና" አብዛኛው አባል በነጠረ በሰከነና በሰላ አንደበታቸው በወቅቱ ቀደምትና ነባር ሁኔታዎችን አጣጥመው ከአወራረሱ በኋላ የተሠራው "ሕብረ-ብሔር" የትግል ፍሬ "ቅንጅትን" ጠንሰሶ በመውለድ ኢትዮጵዊነት አንገቱን ከመድፋት ቀና ብሎ እንዲኅለብት፤ በጀግንነት ልቆ ልብና አእምሮው በጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ላይ እንዲያነጣጥር የማዕዘን ድንጋይ ሆነ። ወሳኝ ድል ግን አልተቀዳጀንም። ይህ ***"የኢትዮጵያውያን ሲምፖዚየምም"*** በኢትዮጵያውያን ብቻ ተሳትፎ በአንጻሩ የዲያስፖራውን ቀስተ ደመና መውለድ ግድ ይሏል። በዚህ ውስጠ-ኃይል ሂደትም ዳር አድራሽ ቆራጥ የትግል መሪ ብቅ ሊል አመቺ ነው።

የኢትዮጵያውያን ሲምፖዚየም ግዙፍ ኃላፊነትና ትኩረት በሕብረተሰብ አውታር-ግንድ በፖለቲካው ተቋም ላይ ነው። ይኸው ፍፁም ወሳኝ ዘርፍ ደግሞ በይዘትም በቅርጽም ኅብረ-ብሔር ባህርይ የተላበሰና ሌሎች ቀደምት ተቋማትንና አዳዲሶችንም በመፍጠርና በማኅልበት አዎንታዊ ድርሻ የሚጫወት ነው። ይጠበቅበታልም። በመሆኑም የፖለቲካው ክንፍ በመለስተኛ ነገር ግን በወሳኝ ደረጃ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ በሕዝቧ ነጻነትና አንድነት የማያወላዳን ማንኛውንም ኃይል ማስተባበርና ማቀፍ ግድ ይሏል። ይህ ጃምቦ የህብረተሰብ ክንፍ በሕዝብ ርዕቱ ተሳትፎ በሂደት ነባርና ነጠላ ስብሰቦች የኅብረ-ብሔር ባህርይ በስነ ልቦናም ደረጃ የተቀበሉና ለቁሳዊ ህልውናም (ኅብረ-ብሔር) እውን ሆኖ ለመተግበር ፓርቲአዊ ወይም ድርጅታዊ ድንበር መዝለል ግድ መሆኑን ያረጋግጣል። ከዚህ በመነሳት ነገና ከዚያ ባሻገር ለሚደረግውና ለሚጠብቀን የወል ክንዋኔዎች በተለይም ሁለንተናዊ ሕዝባዊ ፖለቲካዊ ተሳትፎዎች በኢኮኖሚዉና በትምህርት ወዘተ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማቆሚያ ለማይኖረው ዕድገትና ልማት፤ ከምንጊዜዉም በተለየ እንዲቀራረብና አንድነቱ ለንፋስ ማስገቢያ የማይገኝለት ክፍተት-አልባ ፍቅር እንዲያኅለብት የማዕዘን አለት ድንጋይ እንዲሆን ግድ ነው። ይህ ሕብረ-ብሔር ቫንጋር-ኃይል የቀድሞ የኢትዮጵያን ሠራዊት አባላት በማሰባሰብ በተለያዩ ግዛቶች መስኅ ከሚፋለመው ከአርበኛው ወገናችን ጐን እንዲሰለፉ በማድረግ ማንኛውንም የባዕድ ጣልቃ-ገብ ጦር ሐገራችንን ከመውረር ለመከላከል ሰፊ ዝግጅትና ረቂቅ ቀመር የተላበሰ ስልትና ስትራቴጂ ያጤኗል። በተለያዩ ቀደምት አስተዳደሮች ተመክሮና

እውቀት ያካበቱ ኢትዮጵያውያንን ያሰባስባል። ይኸን ሁሉ የኃይል ምንጭ እሴቶች (Firepower) በማደራጀት የምንቆጣጠረው እንጂ የማንቆጣጠረው ሁከት ተከስቶ የውጭ ኃይሎች በሰላም አስከባሪነት ስም ሌላው ግዛት ኡጋዴንን ለጥቆ በማስገንጠል እልቂት ሰፍኖ ታሪክ ሆነን እንዳንቀር በቂ ዝግጅትና ጥንቃቄ ከወዲሁ ማድረግ ግድ ነው። አሊያ ግን በአንዳንድ ሃገሮች ዛሬ የምንከታተለዉና የተከታተልናቸው የእርስ በእርስ ግጭቶችና እልቂት ቡድናዊ ወይም ድርጅታዊ የፖለቲካና ጎሳዊ ስብስቦች ዘግናኝ ውጤት ነው። በእጅ ጣቶች ከሚቆጠሩት አንዱ የፍልስጤም ሕዝብ የነፃነትና ሉዓላዊነት ትግሎች ያስተውሷል።

***"...አብዛኛውን ጊዜያችንን፤ ሀብታችንና ጉልበታችንን ለጦርነት በመዘጋጀት ጨረስነው። ለዘሌቄታ ሰላም ምን ያህል ጥረትስ አድርገናል?"*** (ጦቢያ ጥር 1992 ፀጋዬ ገብረ መድህን አርአያ) በታሪካችን ሂዴቶች ህዝባችን በአያሌ መቶ ሺዎች ቁጥር በባዕዳን ጠላቶቹ እጅ ተጨፍጭፏል፤ በተለያዩ ወቅቶች በስልጣን ሽኩቻ አንጻር በተከሰቱ የገገሮች ግጭቶች ወገን በመለየት ጭዳ ሆኖ ያለቀው ሕዝባችን ቁጥር ቀላል አይደለም። አሁንማ ጥፋታችንን በሚሹና ቤንዚን በሚያርከፈክፉ በባዕዳን እኩይ ረቂቅ ሴራ በወያኔና ሻዕቢያ የዉክልና (ፕሮክሲ) ጦርነት አማካኝነት የሚፈጠረው እልቂት ሒትለር ከጨፈጨፋቸው ስድስት ሚሊዮን አይሁዶች በላይ እጅግ የከፋ ነው የሚሆነው። እንዲያውም በዋቢነት በሚጠቆሙ ውስጥ አዋቂ ምንጭ ስድስት ሚሊዮን ሕዝባችን በነዚህ ቅጥረኞች ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ተፈጅቷል። ***ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ብለው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሰኔና ሰኞ እንደገጠመላቸው በጤናማ አዕምሮ አሺጋግሮ መመልከትና ማጤኑ ጨው ለራሰህ ስትል እንዲሉ በጥሞና ይታሰብበት።*** ይህን መሰል ዘግናኝና ለመጸጸት እድል ለማይሰጥ አስከፊ ክስተቶችና ሁኔታዎች በአስተማማኝና በእርግጥኝነት ለመቆጣጠርና ለመጭው ማለፊያና ደግ ዘመን የተስፋ ጭላንጭሎች ጭለማማ ሕልም ሆነው እንዳይቀሩ በፖለቲካው ክንፍ ላይ ወደር-አልባ ጭነት ተከምሯል። ለዚህም ነው ዘለቄታማ ሰላምና እድገት ለማስፈን አዉታር ግንድ የሆነውን የሕብረተሰብ ክንፍ የፖለቲካዉን አካል በሰፊው አቅዶ ማዋቀሩ ግድ የሚሆነው፤ ፍጹም ወሳኝም ነው።

*"...ከሰዎች በፊት በስልጣኔ በራፍ ላይ ደርሰን ከኋላችን የመጡት በአዳራሹ ሲገቡ እኛ አሁንም ውጭ ቆመን መቅረታችንና በልመና የምንኖር መሆናችን የገዥዎቻችን የአፈና ተግባር የማይቀር ውጤት ሆኖ ነው። በህገ-አራዊት እየተመራን የሰውነት ሃብታችንን፣ አእምሮአችንና መንፈሳችንን ታፍነን ኑሮአችንን የምናሻሽልበትን ዘዴ ለመፍጠር አልቻልንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ-ወኔ የነበራቸውና ሐሳባቸውንና እምነታቸውን ማንንም ሳይፈሩ በአደባባይ ለማውጣት የቻሉ ሰዎች በመገኘታቸው ከአፈና ባሻገር ጭራሹን ባዶ አለመሆናችንን ያሳያል።"* (ፕሮፌሰር መስፍን ደቂቀ እስጢፋኖስ) የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የጀግንነትና ጀግኖች ምንጭ ነንና በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በወያኔ ጥይት እየወደቁ ባለበት በዚህ አስከፊ ሰዓት አያሌ ጀግኖቻቸንም በእስር እየማቀቁ ነው። ይህ ፀሃይ የሞቀው ሃቅ የሚያስተጋባው የአደባባይ ሚስጢር ቢኖር ኢትዮጵያችን የጀግና መካን አለምሆኗን ነው። በየአጉራባች ሐገር በስደት የሚንገላታው ወገናችን ከፊሉ ወጣ ገባ እያለ የተቀረው ደግሞ በጠኔም እየተገረፈ የኢትዮጵያን የነጻነትና የድል ቀን ለማየት በዱር በገደሉ ተሰልፏል። ይህን ፀረ-ወያኔና ፀረ-ውስጥ-በቀል ጠላቶችን በሕዝባዊ መሰረት ላይ ማነጽ ከነጻነት በኋላ ለሚሰፍነው ሰላምና መረጋጋት ብሎም ሁለንተናው ማህበረሰባዊ ሰላማዊ ተሃድሶ፣ ግንባታ፣ ልማትና እድገት ለማረጋገጥና ዋስትና ለማስረገጥ ገላጭ ቅጽል አይስፈልገዉም።

**ወፍ በአንድ ክንፏ አትበርም።** በአንጻሩ የሰው ልጅች ስብስብ ማኅበረሰብ ለሕልውናው፣ ለዋስትናውና ከልማት ጋር በተቆራኘ የእድገት እንቅስቃሴዎቹን ለማከናወንና ምኞቱን ለመተግበር ብሎም **የሰላም አየር በመተንፈስ ለመብረር ጤናማ ህብረ-ብሔር ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ክንፎች ያሻዋል።** ሳይደግሱ አይጣሉ እንዲሉ ዛሬ በስደት ህይወት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖረው ኢትዮጵያዊ/ት ዜጋ ኢትዮጵያን በፖለቲካውና በኢኮኖሚው አውታር ዘርፎች፣ በሂደትና በተዋረድ በሌሎችም ንዑስ ማህበራዊ ዘርፎች (በትምህርት በባህል... ወዘተ) ለመታደግ በቂ ንዋይ፣ ቁስአዊ አቅም፣ ዕዉቀትና ተመክሮ ታድሏል። ቁምነገሩ እነዚህን እሴቶች በሥርዓትና በዘዴ የወል ጥቅሞች ላይ ለማዋል በወል

ማቀድና በወል ተልሞ መተግበር ነው። በፖለቲካው ክንፍ እንደሚዋቀረው ህብረ-ብሔር ስብስብ በኢኮኖሚውም መስክ ብቁ የሆኑ የኢትዮጵያን ልጆች በማሰባሰብ (በስምፖዚየሙ) እውቀትና ተመክሯቸውን ከወዲሁ ለወል ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ኢትዮጵያን ለመታደግ በሰፊውና በጋራ ለመስራት ቅድመ ዝግጅት ለመጀመር በዜግነት የውዴታ ግዴታ ቃል በመግባት መሰባሰብ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህን ጠበብት ኢትዮጵያውያን በኢኮኖሚው ዘርፍ አንቱ የሚያሰኝ ዕውቀትና ተመክሮ ላዳበሩና ላካበቱ ኢትዮጵያውያን በስምፖዚየሙ ላቅ ያለ ትኩረት የሚሰጠው ወሳኝ ጉዳይም ነው። ለድል እንዲያበቃን በሚዋቀረው እንደ ፖለቲካው ልጥጥ አካል (political extension) "የኢትዮጲያ ሕዝብ አርበኞች ሠራዊት" (ሕዝባዊ ጦር)፤ የኢኮኖሚውም ክንፍ በኢኮኖሚስት ኢትዮጵያዊያን ህልቆ-መሣፍርት የኢኮኖሚክስ ዕውቀትና  ተመክሮ ሊታነጽ ግድ ነው። የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ በነዚህ ሁለት ክንፎች ራሱን በአስተማማኝ ቾሎ እንዲበር የሁሉም ዜጋ ሕብረ-ብሔርነት በመደጋገፍ እንዲቀናጅና በምርምርና ጥናት የተደገፈ ሁለንተናዊ  ትግል ያረፈው በዚህ ትውልድ ጫንቃ ላይ መሆኑን መረዳት ብልህ ግንዛቤ ይሰጣል።  መጭው ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን በሂደት እንዲንከባከብ ግድ ከሆነና ከአመንበት!! ያልያስያዝነውንና ያላስጨበጥነውን በዳሰሳ ወይም በጭፍን ኢትዮጵያዊነትን መንከባከብ አይችልም። ኢትዮጵያዊነት የሰው ልጅ ለሰው ፍቅር ነው፤ ኢትዮጵያዊነት ፍሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት እውነተኛነት ነውና!!

ማንኛውም ማህበረሰብ ዳር ድንበሩን የሚያስከብርና የሕዝቡን ደኅንነት የሚያረጋግጥ ፈርጠም ያለ "ሕዝባዊ ሠራዊት" ለመግንባት ከምንም በፊት ቅድሚያ የሚስጠው ያለምክንያት አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በጅምላ ግድያና በጅምላ ረሀብ እንዲያልቅ (በተለይ አማራው) በስውር ከወያኔ ጋር የተደረገ ዓለም-አቀፋዊ ሤራ ስምምነት ለመኖሩ መገንዘብ ለእኛ ለሰለባዎቹ ሚስጥር አይደለም፤ *የዳርፉር ጀኖሳይድና* በቅጥረኛው የወያኔ ሠራዊት ብዙውን የሶማሌ ዜጎች ሲገደሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉዳዩ በአለም-አቀፍ ደረጃ ለአለም ፊርድ ቤት እንዲቀርብ የሰብእና ተብዬ ተቋማት ለዓለም ብዙሃን ዜና ስርጭት አውታሮች (ጋዜጦችና ኢንተርኔቶች) የአለም ህዝብ ግንዛቤ እንዲያገኝ ሲያደርጉ፤ በአንጻሩ በአስር እና መቶ ሺዎች እንዲሁም ከዚያ በላይ (እንደ አቶ ገብረ መድህን አርአያ ዋቢነት ስድስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ተገድለዋል) በወያኔ አግዐዚ ልዩ ጦር ለሚጨፈጨፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አንድም አስታዋሽ አልተገኘም። ተብየ የሰብዕና፣ የሰው ልጅ መብት ተከራካሪና የዓለም ፍርድ ተቋማት (ጄኖሳይድና የጦርነት ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ) ምን አሉ? ምንስ አደረጉ? በኢትዮጵያውያን ላይ ዓለም አቀፍ ወንጀሎች ሲፈፀሙ በጋምቤላ፣ በአማሮች (በአርባጉጉ፣ በበዳኖ፣ ጉራፋርዳ)፣ በኦሮሞው (በጌዴዎ)፣ በሱማሌ... ወዘተ ወገኖቻችን ሲጨፈጨፍ ዝምታ የመረጡት ከደሙ ንፁህ ነን ለማለት ነው? እንዲያውም በንቁ ተባባርነትና ተሳትፎ በኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀነባበረ ወንጀል በረቀቀ ስልታዊ ዘዴና ገጽታ እየተፈጸመ ነው። ትዝ ቢለን፤ ከዓለም አቀፍ ገንዘብ ተቋማት (የገንዘባችን ምንዛሬ ዋጋ እንዲያሽቆለቁልና ለብዙሀን ረሀብ በመዳረግ)--በወላጅ አልባ ምክንያትና ሌላም ፈጠራ በሺና በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ሕፃናትን በየአመቱ ሕገወጥ በሆነ መንገድ በማሳደግ (Adaption) ሽፋን ባዕዳን ቢሮ ከፍተው የሚያጓጉዙት፤ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ እህቶቻችንን በሥራ ፍለጋ ሰበብ ከሀገር ማስኮብለል (Human Trafficking) ወንጀሎች፤ እስከ ቅርቡ ትላንትናው በምግብ ደህንነት ሰበብ በራሳቸው ጉባኤ፤ በፈጠሩት የኢትዮጵያ መንግሥት ስም (መንግሥት በኢትዮጵያ የለም!) አሳትፈው (ኢትዮጵያውያንን ከአካባቢያቸው በማፈናቀል መሬታችንን ለባዕዳን ሲሸጥ፣ ሲያኮናትርና የብዙሃን ጭፍጨፋ ሲፈጽም ጭው ያለ ዝምታ እያሰሙን)- ይበልጥ በወንጀሉ እንዲገፋ ሎጂስትክ ሊሰጡ ሸር-ጉድ በአደባባይ ዛሬም የምንመሠክረው ሐቅ ነው። ከዚህ በላይ መተባበር ምን የቀረ አለ? ምናልባት ወታደር ከወያኔ ጎን ማሰለፍ ካልሆነ በቀር! ያም ቢሆን ጊዜ የሚያጋልጠው ነው። አቶ አበበ ገላው ያጋለጠው ወንጀለኛውን የወያኔ መንግስት ቁንጮ አይደለም። ሌባን ሌባ ቢሉት ስድብ ወይም ውርደት አይደለምና! ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በቅጥረኛው ጉዳይ አስፈጻሚ ጐሬላ የወያኔ መንግስት ጋር ያለውን ጥብቅ ቁርኝት የሚያጋልጥ የቁርጥ ቀን ልጅ እርምጃ ነው። አቶ አበበ ገላው ዓለም አቀፍ ወንጀል (ጄኖሳይድ) በኢትዮጵያዊነት ላይ ይፋ መታወጁን እንዳወቅንባቸው ለተሳታፍዎቹና ጋባዥ መንግስታት እንዲያውቁት ለኢትዮጵያውያን የወል ነጋሪት ጋዜጣ

ነበር። አከተመ፤ ሚና መለየትና ቁርጥ መስዋዕትነት አሁን ነው። ኢትዮጵያዊነት ወይም ወያኔነት፤ በቃ! የጄኖሳይድ ወንጀል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተፈጽሟል፤ እየተፈጸመም ነው። ለዚህ ወንጀል ተዋንያን ግለሰቦችና መንግስታት በአለም ፍርድ መድረክ ፍትህ ለመጠየቅ መረጃዎች በጥናትና ምርመራ ስራዎች ከወዲሁ ማመቻቸት ቢዘገይም ግድ ይሏል። ይህ በእንዲህ እንደተያዘ ይህን የተቀነባበረ አለም-አቀፍ ሴራ መንስኤ-ሰበብ በሚከሰት ማህበራዊ ቀውስ ለማጋለጥና በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ሕዝባችን በአስቸኳይ እራሱን ከባሰ ዕልቂት እንዲከላከል ለማድረግ "ሕዝባዊ የአርበኞች ሠራዊት" መዘርጋት የኢትዮጵያውያን ሲንፖዚየም ተቀዳሚና አብይ ተልእኮ ሊሆን ይገባዋል። በዚህ በተቀነባበረ ሴራ የሚቆስልና የሚሰደድ ወገናችንን ለመታደግ ደግሞ ዛሬ በምናዋቅረው ሕዝባዊ ድርጅት ውስጥ ድንገተኛ ደራሽ እጓለ ግብረ ኃይል (National Emmergency Task Force) በመሆን ሎጆስቲካዊና የሰው ሀይል በማቀናጀትና ማኔጅመንት በሰፊው በማጤንና ቀድሞም ዝግጅቱን በጥልቀትና በስልት ተልሞ በማቀድ፣ በመቀመር ለተግባራዊነቱ ሕዝብን ያሳውቃል፤ ያስተባብራልም። ህዝቡም እንዲሳተፍ ያደርጋል። በዚህ የስብእና እንቅስቃሴ ውስጥም የሃይማኖት ተቋማትና ምእመናን ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል።

እንግዲህ "የኢትዮጵያዊያን ሲንፖዚየም በመሰረታዊ ዓላማው ዜጎች ብቻ (ኢትዮጵያውያን ብቻ) ለስብእናቸው፤ ለመንፈሳቸውና አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ኑሮአቸው የሃገራቸውን ዳርድንበር በማስከበርና የእያንዳንዱን ግለሰብ መብትና ግዴታ በህግ የሚያስከበርና የእያንዳንዱን ነገድና ጎሳ ወደፊት በሚረቀውና በህዝበ ውሳኔ በሚፀድቀው ህገመንግስት በማስከበር ጠንካራ ሕበረተሰብና ጠንካራ ግለሰብ በማነጽ በሁለገብ ትግሎች "ኢትዮጵያዊነት ከኢትዮጵያውያን፤ በኢትዮጵያውያን፤ ለኢትዮጵያውያን" ሕዝባዊ መርህ ላይ ተመርኩዞ የመሰረት ድንጋይ ለማኖር ነው። የኢትዮጵያዊነት ጽንሰ ሀሳብ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደሰባት ሺህ በሚጠጋ ምእተ ዓመታት ያዳበረው ባሕል፤ ታሪክ፤ አበው እምነቱና ሀይማኖቱ በሂደት የዥንጉርጉሯ ግን ከመሳ ለመሳ ዘነገደ ኢትዮጵያ ቅይጥ ንጥረ ነገር ውጤት ነው። አያሌ ሌሎች የታሪክና ማህበረሰባዊ ሳይንስ ሊቃውንት ኢትዮጵያውያን በብቃትና ዕውቀታቸው አኳያ አስተማማኝ በሆነ ይዘቱ ታሪክና ባህል በአማከለ በፍልስፍና ደረጃ ስለ ኢትዮጵያዊነት ብቸኛ ጽንሰ ሀሳብ እንደሚያስተምሩን ተስፋ እናደርጋለን።

***በተመስጦ "ኢትዮጵያዊነትን" በአይነ ህሊናችን ትኩር ብለን በማየት የኢትዮጵያን ድህረ ሁለትሺ ምእተዓመት በየዘመኑ ለማክበር ሰናስብ ዘርፈ ሰፊ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ የዜግነት ሃላፊነት ያረፈው በዚህ በእኛ ትውልድ ትከሻ ላይ ነው። በአጥንታችን ሥር እስኪያበቅል መደጋገም ያለበት አደራ ነው።*** በኢትዮጵያ-አምላክ ፈቃድ ይኼ ትውልድ የታደለውን ጸጋ ሲቃኙት እውነትም ኢትዮጵያ ሀገራችን የቃልኪዳን ሀገር ነች ያሰኛል። በስደት ህይወት ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነትን ከብረት በላይ በጠነከረ ማእዘን በተሃድሶ በማነጽ ኢትዮጵያን **"የሃይል ምንጭ ቤት"** ለማድረግ ያካበተው እውቀት፤ተመክሮና ሀብት ለማመን ይከብዳል። በምንያያዘውና በተያያዝነው የኢትዮጵያ ድህረ ሁለት ሺህ ምእተዓመትና ድህረ ጥቂት አስርተ ዓመታት ይሄ ትውልድ ኢትዮጵያ ሃገራችን ማንም ሃገር በታሪክ ያላስመዘገበዉን ሁለንተናዊ ማኅበረሰባዊ ግንባታ እድገትና ልማት እርከን እንድትነካ የሚያስችልና የሚያበቃ ክምችት ሐይል ነው። ይህ ትውልድ ዛሬ ነገ ሳይባል በየሙያ ዘርፉና ዝንባሌው እንዲሰባሰብና ምን ማድረግ እንዳለበት ከወዲሁ እንዲመክርና እንዲዘክር በኢትዮጵያዊያን ሲንፖዚየም መድረክ በሚፈጠሩት ዲፋክቶ ተቋማት ጥላ ስር እንዲሰባሰብና እንዲደራጅ ማድረግ ቀዳማዊ ጉዳይ መሆን አለበት። በዚህ መልኩ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን ግዴታ ይወጣል፤ ሁሉም እሴቶች (ዜጎቻችንም) በስርዓት በማቀናጀት ኢትዮጵያዊነት በሁለንተናዊ ማህበረሰባዊ ዘርፎች እንዲዳበር ግድ ይሏል። "YOU NEVER KNOW WHAT YOU CAN DO UNTIL YOU TRY IT"

እነዚህ ዲፋክቶ ተቋማት ለምሳሌ የትምህርት ዘርፉ ቀደምት አንጋፋ መምህራንና በሙያው ላይ የተሰማሩ በተለያዩ ሃገሮች የሚገኙትን ኢትዮጵያዊያን ያሰባስባል፤ ስርዓተ ትምህርት በየትምህርቱና በየደረጃው የኢትዮጵያን ታሪክና ባህል ባጣጣመና ሳይንስ፤ ፍልስፍና እና ቴክኖሎጂ ጋር በተሳሰረ መሰረት መንደፍ። በትምህርቱም ዙሪያ በመዋእለ ሕጻናት፤ በአንደኛ ደረጃ፤ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ፤ በሁለተኛ

ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት መስክ ምርምርና ጥናትንም ያካተተ አብይ ዝግጅቶችና እቅዶች መንደፍ ይጀምራል። የግእዝ ትምህርትም በተቋም ደረጃ እንዲዋቀር ሰፊ ዝግጅት ያጤኗል። የማንኛውም ህብረተሰብ ማህበራዊ ልማትና ሥልጣኔ አውታር መሰረቱ ትምህርት በመሆኑ በዚህ በኢትዮጵያዊያን ሲምፖዚየም ለሚጠነሰሱ ዲፋክቶ ተቋማትም የባለሙያ ምንጭም መመሪያ ምልክትም “GUIDING POST” ትምህርት እንደሚሆን ግልጽ ነው። በእኩይ ጠላቶቻችን ሤራ የወላለቀውና የፈራረሰው ሥርዓተ ትምህርት እቅድና ዝግጅቱን በማስመልከት በምን ቃላት እንደሚያጎሉት እንጃ!! ሌሎችም ተቋማት እንዲሁ በሂደትና በተዋረድ የሚገባቸውን መስመር እንዲይዙ ይሆናል። ለዚህ ነው በተያያዝነው የኢትዮጵያ ድህረ ሁለት ሺህ እስራ ምዕተ ዓመት የዘመን አድማስ ባሻገር፤ የኢትዮጵያ-አምላክ ለሕዝቧ ባደለው የተፈጥሮ ሀብትና ፀጋ (ዛሬ በዘረፋ ሳያልቅ ካዳነው) የልጆቿን እውቀትና ተመክሮ በማቀናጀት ጠላት ዐይኑ ደም ይለብሳል እንጂ ኢትዮጵያን የአፍሪካ ጃፓን ለማድረግ ሁሉም በእጃችን መዳፍ ስር ነው። ካወቅንበትና ይህን ለማየትና በቅን ለማወቅ ከተነሳሳን የማይሆን ነገር የለም። በአንድ ወቅት ሊቅ ኢንጂነር ቅጣው እጅጉ ስለኢትዮጵያ ፕራግማቲካል ራእይ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምን እንደሚታያቸው ሲመልሱ ***“በባዕድ ሃገር እንደምንሰራው በሙያችን ተሰማርተን ለሃገራችን ብንሰራ በአሰር ዓመት ውስጥ በሃገራችን የሚያመርቅን መሠረት በማኖር የኢኮኖሚ ግንባታና ሁለንተናዊ ልማት ማስመዝገብ ይቻላል።”*** ነው ያሉት። ለዚህም ነው <u>**“የኢትዮጵያዊያን ሲንፖዚየም”**</u> ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ከሚደረገው ሁለገብ የነጻነት ትግል ጎን ለጎን በግንባታና ልማት ዘርፎች ከህዝብ በህዝብ ለህዝብ ያላሰለሰና ያልተቆጠበ ጥረትና ተሳትፎ እንዲደረግ መንደርደሪያ መድረክ ነው የምንለው። የኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ዘርፍ አስተማማኝ ደረጃ ላይ መድረስ የሚያስቀናቸው ታሪካዊ ጸረ ኢትዮጵያ ሀይሎች የተፈጥሮ ሀብቷን በሰፊውና በፍጥነት ከመመዝበር በተጨማሪ ለልማት፤ ለእድገትና ለዚህም ለዚያም ሰበብ በኢትዮጵያ ስም “ሕዝቧንና ሀገሪቷን ለማይወክል ወያኔ ለተባለ ወራሪ ቅጥረኛ ቡድን” አገዛዙን እንዲያጠናክር ከአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት የሚጎርፈው ብድር ጣጣው ብዙና ረቂቅም ነው። ይህ መሰሪ ስሌት በአሉታዊ ጎኑ የኢትዮጵያ ሀገራችንን የወደፊት እድገት ሆን ተብሎ ለመጎተት የሚሸረብ እኩይ ተግባር ነው። ታሪካዊ ጠላቶቻችን በወያኔ እንደራሴነትና አማካኝነት ያገኙትን ነጻ የምዝበራ ጉዞ ማቆሙ ግድ ነው። እድገት በዘረፋ ከተሟጠጠ እሴትና ሀብት አይጀመርምና የእጅ አዙር የኢኮኖሚ ባርነት ካልተመኙ በስተቀር በራስ በመነሳሳት መተለምና ማቀድ፣ መምከርና መዝከር አማራጭ አይገኝለትም።

በስደት ያለው ትውልድ በኢትዮጵያውያን ሲምፖዚየም አማካኝነት በሃገራችን ላይ በወያኔና በታሪካዊ የሃገራችን ጠላቶች ስለሚደርስብን ደባና የዐዞ እንባ ረጪ እኩይ ባህርያት ግንዛቤ ካገኘ በኋላ በራሱ ላይ የባህሪ ለውጥ በማምጣት ሁለገብ ድላችንን ለማቅረብ፤ ሀገራችንን ከወያኔና ከታሪካዊ ጠላቶቻችን በልመና ሳይሆን በመራራው ትግላችን መልሰን በእጃችን የምናስገባው በአንድነት ስንታገል መሆኑ ገብቶት ልብና አእምሮው ሲጣጣምና ሲተሳሰር፤ ከሀገር ቤቱ ትወልድ ወገናችን በአካልም በስነልቦና ንክኪትና ማለፊያ ግንኙነት በሂደት ለማጎልበት በጋራ የሚዋቀርና የሚደጎም የወል ብዙሃን ዜና በዲፋክቶ ተቋም ደረጃ መመሥረቱ  (የሬድዮ ስርጭት፣ የእትመትና ቴሌቪዠን በሥራ ክፍፍል አኳያ) ወሳኝ ሚና አለው። ሚዲያው ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን በተለያዩ ቋንቋዎች ሐገር ቤት በአየር የሚበተነው የሬድዮ ሰርጭት፣ በኢትዮጵያዊያን ሲምፓዝየም በሚጠነሰሰውና በሚዋቀረው ዲፋክቶ ብዙሐን መገናኛ ተቋም ውስጥ በመካተት በተለያዩ አህጉራትና ግዛት የሚገኘውን ወገን ለንቁ ማኅበራዊ መቀራረብና ተሳትፎ ለሁለገብ ትግሉ፤ ለዘርፈ-ብዙ ታህድሶ፣ ግንባታውና ዳግም ግንባታው (Construction and Reconstruction) የኢትዮጵያ ሕዝብ እንቅስቃሴዎች በየመስኩ በከፍተኛ ፍጥነት እንዲሸከረከር የሚያደርግ የሞራል ሞቶር ይፈጥራል። እንዲሁም በስደት ያለውን ኢትዮጵያዊ የትግል እንቅስቃሴዎች በሐገር ቤት ከሚደረጉ ትግሎች ጋር በፍጥነት እንዲቀናጅ ይረዳል። በአንጻሩም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርታዊና ንቃተ ኅሊና የሚያዳብሩ መጣጥፎችን በህትመት ዜና ብዙሃን (መጽሔቶችና ጋዜጦች) ሰርኩሌሽን/ስርጭት እውን ማድረግ ንቁና ግንዛቤ ያዳበረ ዜጋ በጥራትም በቁጥርም እንዲጎለብት ይረዳል። በዚህ መልኩ አዎንታዊ የባህርይ ለውጥ የሚያደርግ ኢትዮጵያዊ ዜጋና አንድነቱ በጠነከረ ሕዝብ፤ በጋራ ችግሮቹ በወል ያመፀና በድሉ የጋራ ተጠቃሚ መሆኑን የተገነዘበ ማህበረሰብ ጠላት መግቢያ ቀዳዳ

የማያገኙለትና የማይበረቡረው የዓለት መሠረት ነው። አሊያ ግን ኢምንት ታህል ክፍተት ፈጥሮ መሳይ-አፍቃሪ የኢትዮጵያ ኃይል ጋር በምንም ይሁን በማንም ጭንብል ያጠለቀ እኩይ ሰላቢ ለምንም ቅርበትና ወዳጅነት ፀረ-ኢትዮጵያ ሐይሎችን በብሂል-ጠቀሳና መሰል-መርህ ተብዬ ባዕዳዊ አባባሎች ንክኪት መፍጠር በወገን መሀል እጅግ አሳሳቢነቱና አደገኛነቱ አያጠራጥርም። በየመጣጥፎቹ የምናነባቸው ሙገሳዎች፤ ከምንታዘባቸው ጨብጥ ዕለት ተዕለት ገጠሜ ሁኔታዎች ጋር እጅግ ይጻረራሉና ወደፊት ያልተጠበቀ የወገን መቃቃር ይፈጥራል። ክቡር የሰውን ልጅ የሚያወድስ ብሂል የሚያስተጋባ የሰውን ልጅ በባርነት ቢይዝ ትምህርቱ ምንድርነው? የወያኔ ወዳጅ የኢትዮጵያ ወዳጅ ሊሆን አይችልም። ለመሆኑ ፈረንጅ "ከብርማ ሳህን ሲበላ" እኛ እንድናገሳ የሚሰብኩን የዲሞክራሲያ ደቀ መዝሙርት በመረጣችሁትና በተጠመቃችሁበት መንደር ስበኩ እንጂ እየፈረሰችና እየደማች ያለች ሐገሬን ከነጻነትና ከሉዓላዊነት ሁለንተናዊ ተጋድሎ ዝንፍ እንድንል አንሻም። በአፋችን ልጓም ባይኖር ስለተብዬ ዲሞክራሲ ምን ማለት እንደምንችል አዲሶቹ ፈረንጆች የሚስቱት አይመስለኝም። ለሁሉም ጊዜ አለው ብሏል ጥበበኛው ሰለሞን። ዛሬ የኢትዮጵያ ትግል ማተኮር ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ነጻነትና የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበርና ማስከበር ላይ ብቻ ነው፤ ሌላው በኋላ ይደርሳል።

ጀኔራል ኃይሌ መለስ የውጪ ሐገር ፖለቲካዊ አጋር መንግሥት ወዳጅነት ማጣት ችግራችን እንዲታስብበት በገሃድ ሲማጸኑ *"ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት እና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስራች፤ በጸረ ቅኝ አገዛዝ ተጋድሎዋ የታወቀችና ለብዙ ሐገሮችና ሕዝቦች ነጻነት ግንባር ቀደምት ሆና ስትከራከርና ስትፋለም የኖረች፤ የሐገሮችና ሕዝቦችን ብሔራዊ አንድነትና ሕልውና የምታከብር፤ ለዓለም ሰላምና ብልጽግና የቆመች፤ ዓለም አቀፍ ውሎችንና ስምምነቶችን ከሚያከብሩት ግንባር ቀደም ሐገሮች አንዷ የሆነች ታላቅ ሐገር ሆና ሳለ እንደዚህ ያለ የተቀነባበረ ዘመቻ እየተካሔደባት አንድነቷ ሲናጋ ሕዝቧ በዘር ተከፋፍሎ በግፍ ሲጨፈጨፍና ሲሰደድ ለምን እንደዚህ ይደረጋል? ብሎ ድምጹን ያሰማላትና ቁም የተከራከረላት እንደማስረጃ የምንጠቅሰው አንድም ሐገር ወይም መንግሥት አለመኖሩ ብዙ ትምህርት ሊያስተምረን ይገባል።"* (ኢታር ኤፒርል 1998) ይኸ ችግር በእርግጥ ከፉኛ ጎድቶናል። በሬ ከአራጁ እንዲሉ ጎጅ ጠላቶችን በእጅጉ እንድንወዳጅ የአዲሶቹ ፈረንጆች መጣጥፎአቸውን በአጽንኦት ማጤን ግድ ይሏል። በፖለቲካውም ይሁን በኢኮኖሚው ወይም በወታደራዊ ይሁን በንግድ መስኮች ቢቻል የአንዱ ሐገር ሕዝብ ከሌላው መቀራረብ የረጅም ዘመን የመንግሥት ተብዬዎች ስፊ የቤት ሥራ መሆን ሲገባው የእኛ ቀደምት አስተዳደሮች ያቆዩልን ግን አሳዛኝ ግንኙነት ነው። መቃብራችንን ከሚቆፍሩልን ጋር ነበር። በመሆኑም አንዳንዶች ዛሬ ይኸን አሳዛኝ ድርጊት በተለየ ገጽታ ስያስተጋቡ እየደማች ያለች እናት ሐገራችንን ይበልጥ ስለምናሳዝን ይታሰብበት። እነዚህ ወዳጅ ተብዬዎችን የጎሪጥ በሚመለከቱ ሌሎች ሕብረተሰቦችና መንግሥታት ዘንድ ኢትዮጵያን ከምር ለመወዳጀት ይቸገራሉ። የኢትዮጵያዊያን ስምፖዚየም እውን ለማድረግ በሚደረገው የሀሳብ መንሸራሸር ስብዕና የሚሰማቸው ዲፕሎማቶችና ሕግ ጠበብት ታላላቅ ኢትዮጵያውያን አዕምሮ ጓዳ ይኸ ቁልፍ ጉዳይ ሕያው እንዲሆን ይጠይቋል። የሐገራችን ተጨባጭ ሁኔታም የሚያስተምረን ይኸንን ሀቅ ነው። ተመሳሳይ ስህተቶችን መደጋገም ትምህርት አድርጎ መውሰድ ብልህነት የጎደለው ያሰኛል፤ መጠንቀቅ በተጠንቀቅ!!! ዛሬ በገሃድ እንደምንመሰክረው ጡንቻቸውና አንድነታቸው በሳሱ ሕዝቦች ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዓለም አቀፍ ወንጀሎች እውነታ ነው። በጀሮ ዳባነት ወይም ሌላ ምክንያት ከእውነት በመራቅ ትውልድን ማደናገርና ማሳት ከኢትዮጵያዊነት አይጠበቅም። እንደ ቀደምት አያቶቻችንና ወላጆቻችን ብልኅነትና ጀግንነታቸው ውርስ ቅርሶቻችን የመሆናቸውን ያህል በእኛም ሕይወት እውነተኛነት መተግበሩ ግድ ነው። ሳንመረምርና ሳናነጥር የማንንም ቱልቱላ "ዲሞክራሲያ ኩምባያ" ዜማ አናስተጋባም። ነፃነታችን ተገፏልና! ሉዓላዊነታችን ተናግቷልና! ቅድሚያ ለነፃነታችንና ለአርነታችን! ቅድምያ ለሉዓላዊነታችን! የተቀረው በሂደት ቦታውን ይይዛል!!! ነፃነት የሌለው ሕዝብ ሰላም የለውም!! ነፃነት የሌለው ሕዝብ ፍትሕና ሕግ የለውም!! ዲሞክራሲ ዛሬ እንደምንመሰክረው "አብስትራክት" ማደናገርያና ማዘናጊያ ፅንስ ሐሳብ ነው። ያሠፈሰፈው ፀረ-ኢትዮጵያ የጠላት መንጋ ጊዜ ጠብቆ የሚያዋክበን ጭራቅ ለመሆኑ ኢምንት አንጠራጠር። ብልህ ሕዝብ ስህተቶችና ጥፋቶችን ከጊዜ አድማስ ባሻገር በማነጣጠር ይገነዘብና ይዘጋጅላቸዋል እንጂ ከተከሰቱ

በኋላ መማር ለፀፀት መሆኑን ያውቃል። ያውም ለሕያውነት ዕድሉ ካለ!! ለዚህ ነው ጠላትን በጥልቅ፤ በጠባቡና በነጠረ የወል ግንዛቤ ኖሮን በሁለገብ መንፈስ ለመፋለም እንድንችል የሰከነ የስልጡንነት ባሕርይ የተላበሰ "ሕዝባዊ ውይይት" (ዲያሎግ) በኢትዮጵያዊያን መካከል ብቻ እንዲኖር በኢትዮጵያዊያን ሲምፓዚየም ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ የምንጥረው። የሕዝብ ነፃነትና ሐገራዊ ሉዓላዊነትን በአስከበሩ አፄዎች አገዛዝ ስር ነበር እነ አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ዲሞክራሲያ በሕይወታቸው በመኖር ጎደለም አልተዛነፈ በምድረ ኢትዮጵያ የነበረው፤ የቅርቦቹ አፄዎችም ተምሳሌነቱን ተከትለዋል፤ ዛሬ ማንም በመደለል እንድንገበያይ የሚቀርብ የውጭ ሸቀጥ ሊሆን አይችልም። ዲሞክራሲ የነፃነት እምንት ታህል አካል ነው፤ ያውም ዓለም አቀፍ ይዘት ሰጥተን በትርጓሜው በወል ከተግባባን!!

***ኢትዮጵያዊነት የነባር ሀይማኖቶች እምነት፤ ባህልና ታሪክ ተቀያይጠው ነጥሮ የወጣ የኢትዮጵያዊያንና የሕዝቧን ሉዓላዊነት በደምና አጥንቱ ያስከበረ ፍልስፍና ነው። ኢትዮጵያዊያን ሊቃውንትም በቅርጽና በይዘት እንደምያሰፉት ምኞትና ጸሎቴ ነው።*** አዎን እደግመዋለሁ!! ኢትዮጵያዊነት ከኢትዮጵያዊያን፤ በኢትዮጵያዊያን፤ ለኢትዮጵያዊያን ነፃነትና ሉዓላዊነት፤ ለዳግም ግንባታና ግንባታ ሁለንተናዊ የአለት ድንጋይ መሰረት ነው። የወደፍቱን ወርቃማ ድኅረ አሥራ ምዕት ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመናፈቅ አልፎ በሕይወቱ እንዲኖረው ከተፈለገ ሁሉም ዜጋ እንደአቅሙና ችሎታው በሕብረተሰባችን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች በንቁነት ለመሳተፍ እንዲችል ካሁኑ ከጠባብ የፖለቲካ ድርጅት አጣብቂኝ በመላቀቅ ሕብረ-ብሔር ኢትዮጵያዊነትን ማነጽ ለድርድር የሚቀርብ አይሆንም።

የኢትዮጵያዊነት ዲ.ኤን.ኤ በንጥረ ነገርነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፎ እስከዛሬ ዘልቋል። ነገር ግን አንድ ሀቅ ፈጦ ያየናል፤ ይኸውም በስደት፣ በጎጠኛ ፖለቲካና በፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች እኩይ ተግባር ትውልድን ለማያያዝና ለማቆላለፍ የኢትዮጵያዊነት ዲ.ኤን.ኤው ፍሳሽ ጅረት ቅጥያ ጉዞ የሚያሳስብና ከወዲሁ ትኩረት ካልተደረገ አስቸጋሪ የትውልድ ክፍተት በመፈጠሩ ፍፁም ባዕድ ባሕል ተላብሶ ከሚመጣው ጋር በመጋጨት የጥንቱ የጠዋቱ ኢትዮጵያዊነት ደብዛው እንዳይጠፋ ይታሰብበት ይሏል። የትውልድ ተሀድሶ ጉዳይ በእጅጉ አሳሳቢ ነውና!!! በነባር ሀይማኖቶቿ፣ ባህሎቿና ታሪኳ ለዘመናት የምትታወቀው ኢትዮጵያ፤ በአሁኑ ጊዜ ከቁጥጥር ውጪ ለመጤ ቀዋስ ባህሎችና እጅግ አደገኛ ለሆኑ ማህበረሰባዊ ደዌዎች ለተጋለጠው ትውልድ ልዩ የተሐድሶ ትኩረት በመስጠት የኢትዮጵያውያን ሲምፖዚየም ሌላኛው አንጋፋ ግዴታው መሆን ይገባል እንላለን፤ ***ኢትዮጵያ ዥንጉርጉር ትሁን እንጂ ኢትዮጵያዊነት የነጠረ ወጥ የኢትዮጵያ ብቻ፣ ለምዕተ ዓመታት በሂደት ጎልብቶ ያደገ ኅብረተሰብ ውጤት ልዩ ፍልስፍና ነው።*** ለዚህ ነው ለዘመናት ኢትዮጵያችን በዓለም መድረክ ጎልታ የታየችው። ለዚህም ነው ለነፃነቱና ለዳር ድንበሩ ቀናኢ ሕዝቧ ላይ የተቀናበት!! እንዲጠፋም የተዶለተበት!! አዎን!!! ኢትዮጵያዊነት ከኢትዮጵያውያን፤ በኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያዊያን!!! የአያት ቅም አያት ጀግኖቻችን አጥንት እሾኽ ሁኖ ለትውልድ ትውልድ እንዳይወጋን አደራ!!!

*"ወርቃማው ዘመን በስተጀርባችን የቀረው (ያሳለፍነው) አይደለም። ከፊት ለፊታችን የሚገኘው ነው። ወርቃማው ዘመን የማህበራዊ ሥርዓት ተጠናቆ መፈጸም ማስረጃ ነው። አባቶቻችን አላዩትም። ልጆቻችን አንድ ቀን ይደርሱበታል። የእኛ ሚና መንገዱን መጥረግ (ማሳመር) ነው።"* (ጦቢያ ቅፅ 7 ቁጥር 6፤ 1992)

በኢትዮጵያ አምላክ አዝማችነት፤ በዛሬዪቷ ኢትዮጵያ ጅግኖች አርበኞቻችን ገድል የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ይከበራል።

ነፍጠኛው ቅስአ

ዘእምነገደ ኢትዮጵያ